# በሰሜን ጎንደር እና አካባቢው በተፈጠረው ሁከት ህይዎታቸው ያለፈ የፀጥታ ሃይል አባላት..



አዲስ አበባ ፣ ሃምሌ 12 ፣ 2008 (ኤፍ ቢ ሲ) በሰሜን ጎንደር እና አካባቢው የተፈጸመውን ህገ ወጥ ድርጊት ሁሉም ክልሎችና ሁለቱ የከተማ አስተዳደሮች አውግዘዋል።

ክልሎቹ በድርጊቱ ንጹሃን ዜጎችና በጸጥታ ሃይል አባላት ላይ በደረሰው የህይወትና የአካል ጉዳት የተሰማቸውን ጥልቅ ሃዘንም ገልጸዋል።

በአካባቢው ባለፈው ሳምንት የተፈጠረውን ሁከት ተከትሎ የፀጥታ ሃይል አባላት ወደ ስፍራው በመንቀሳቀስ ደርጊቱን ለማስቆም ጥረት አድርገዋል።

በዚህ አጋጣሚ በተፈጠረ ሁከትም 11 የፀጥታ ሃይሎች ህይዎታቸው አልፏል።



በግጭቱ ህይወታቸው ካለፉት የፀጥታ ሃይሎች መካከል ዘጠኝ የፌደራል ፖሊስ
አባላት የሚገኙበት ሲሆን፥ የስም ዝርዝራቸው እና የትውልድ ስፍራቸው እንደሚከተለው ቀርቧል።

1. ኮማንደር ሃለፎም አዳነ እንደሻው (ፀለምት - ትግራይ) (የተስተካከለ)

2. ሳጂን አለሙ መላኩ እንኳንሆነ (ደባርቅ - ሰሜን ጎንደር)

3. ኮንስታብል ኤቢሳ ኢታና አብዲ (ቄለም ወለጋ)

4. ሳጂን ናስሮ ምሹሮ እስማኤል (ደባርቅ - ሰሜን ጎንደር)

5. ረዳት ኢንስፔክተር አህመድ ሁሴን አህመድ (ስልጤ - ደቡብ ክልል)

6. ምክትል ሳጂን አብዲሳ አለሙ ዳሮምሳ (ም/ሸዋ)

7. ምክትል ሳጂን አትሎግ አሰፋ አበራ (ታች ጋይንት - ደቡብ ጎንደር)

8. ረዳት ኢንስፔክተር አደም አብዱላሂ ማኡ (ሊበን - ሶማሌ ክልል)

9. ምክትል ሳጂን ብርሃኑ ሱሊቶ አበሜ (ሃድያ - ደቡብ ክልል)

ከላይ የተጠቀሰው ግጭት ህይዎታቸው ያለፈ የፌደራል ፖሊስ አባላት ስም ዝርዝር ሲሆን፥ በተነሳው ግርግር ህይዎታቸው ያለፉ የሌሎች ሲቪል ዜጎችን ዝርዝርም እንደደረሰን የምናቀርብ ይሆናል።